# የጥናት ክፍል፡ የሐዋርያት ሥራ 9፡1-31



**ርዕስ፡ የሳውል የመጀመሪያ የክርስትና የሕይወት ጉዞ**

በዛሬው ጥናታችን በአዲስ ኪዳን ታሪክ ውስጥ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥሎ ትልቅ አስተዋፅኦ የነበረውን የሐዋሪያው ጳወሎስ መለወጥ እና የመጀመሪያ ህይወቱን እናጠናለን፡፡

I. **ሐዋርያት 9፡31** ካነበብክ በኋላ የስገረመህን፤ ያሳቀህን፣ የሳዘነህን፣ ያስደሰተህን ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ በመቀጠልም ክፍሉን ፓራፍረዝ ማድረግ ሞክር (Head)

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች**</u>

1. የሳውል የቀድሞ ህይወት (ከመለወጡ በፊት) ምን ይመስል ነበር? (ሐዋ 22፡3 ፤ 5 ፡34-39)
2. *"በዚህ መንገድ"* ሲል ምንን ለማሳየት ነው?
3. ሳውል ማንን ያሳድድ ነበር?
4. በሳውል ጉዞና የኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ጉዞ አስተያዩ፡፡
5. በዚህ ክፍል ውስጥ የሳውልን የጉዞ ካርታ ወይም የሄደበትን 5 ቦታዎች ዘርዝር፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ ጳወሎስ ለሚስዮናዊ ጉዞ የተዘዋወረባቸውን ሀገሮች ለማወቅ ተዘጋጅ
6. ሳውል ተሸክሞ ይዞር የነበረው ደብዳቤ (ፈቃድ) ምን የሚል ይመስልሃል? በዚህ ምትክ ጌታ ምን አሸከመው?
7. በርናባስና ሐናንያ ለሳውል የመጀመሪያ ህይወት አከባቢ የነበራቸው አስተዋፅኦ ምን ነበር ?
8. የሳውልን መለወጥ ማመን መቀበል ለምን አስቸጋሪ ሆነባቸው?
9. የሳውል የመጀመሪያ ስብከቱ እና የመጀመሪያ ስደቱ ምን ነበር?
10. የሳውልን መለወጥ ለቤተክርስቲያን መስፋፋት ምን አስተዋጽኦ አደረገ? ሐዋ 26:16-18 ሐዋ 22:6-21
11. በዚህ ክፍል መሰረት የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት የተጠሩበት 5 ስሞች ዘርዝር፡፡
12. ሳውል ስለ ደማስቆ ምን ትውስታ ነበረው 2 Corinthians 11:32-33

II. **ዛሬ ከክፍሉ እግዚአብሔር ለግልህ ያስተማረህ ምንድነው (Heart)**

III. **ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ካስተማረን ውስጥ ልንተገብራቸው የሚገቡ ምን ምን ናቸው**(Hand)

ከዚህ ጥናት በኋላ ሜሞራይዝ ልታደርግ የፈለግከውን ጥቅስ ወይም አረፍተ ነገር ጻፍ፡፡

____________________________________________